አማርኛ (ኢትዮጵያ)

# የምግብ ባንክ የቤት ማድረሻ ቅጽ

የዩናየትድ ዌይ ኦፈ ካውንቲ፣ ፉድ ላይፍ ላይን፣ የሲያትል ከተማ እና ሜትሮ አክሰስ በ COVID-19 ወቅት የቤት ለቤት የምግብ ሳጥኖችን ለማቅረብ ደስተኖች ነን። ለአንድ ጊዜ ምግብ ለማድረስ ለማዘዝ ይህንን ፎርም ይሙሉ። እባክዎ ይህ ምግብ የሚሸጥ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ለቤት ጥቅም ብቻ የሚውል ነው።

ወደ ደቡብ ኪንግ ካውንቲ ለማስፋት እየሰራን ሲሆን በአሁኑ ሰአት ግን ወደ ሲያትል ከተማ፣ ሰሜን ኪንግ ካውንቲ እና ምስራቅ ኪንግ ካውንቲ ብቻ ማቅረብ ነው የምንችለው።

በዚህ ጊዜ ይህ አገልግሎት ከፉድ ላይፍ ላይን ከ አስራ አምስት - ሀያ አምስት  ፓውንድ  የሆኑ የተለያዩ ምግቦችን ይሰጣል። የምግቦቹ አይነትም፡ የታሸገ ስጋ፣ የታሸገ ፍራፍሬ፣ የታሸገ አትክልት፣ ፓስታ እና ሌሎች የተለያዩ እቃዎች። እንዳንድ ሳጥኖች እንደ ዳቦ ያሉ ቶሎ የሚበላሹ ምግቦች ወይም ሌሎች ረጅም ጊዜ የሚቆዩ ምግቦች ሊይዙ ይችላሉ። አንድ ሳጥን አራት የቤተሰብ አባላትን ከ ሁለት – አራት ቀን መመገብ ይችላል ተብሎ ይገመታል። በአሁኑ ሰአት በግለሰብ ደረጃ፣ የአለርጂ እና የዳይት ፍላጎቶችን ማድረስ አንችልም። ልዩ የሆነ አለርጂ ወይም ዳይት ፍላጎት ካለ ለፍላጎትዎ የሚሆንን ምግብ ሊሰጡ ስለሚችል በአቅራቢያዎ ያለውን የምግብ ባንክ ያነጋግሩ።

በአሁኑ ሰአት፣ ምግብ የሚደረስበት ጊዜ ክሰኞ እስከ አርብ ቀን ላይ ነው። ትዕዛዙን ከተቀበልን በኋላ በሁለት ወይም ሶስት ቀን ውስጥ እናደርሳለን። ሃሙስ እና አርብ የተቀበልናቸው ትዕዛዞች በሚቀጥለው ሳምንት ይደርሳሉ።በተባለው ቀን ማድረስ ካልቻልን መቼ እንደሚደርስ በኢሜይል እናሳውቃለን።

ድርጅት ከሆኑ እና በዛ ያሉ የምግብ ሳጥኖችን መካከለኛ ስፍራ ለደንበኛዎ ማከፋፈል ከፈለጉ Claire Brown ን በዚህ ኢሜይል clairebrown@uwkc.org ያናግሩ።.

እባክዎ ይህ ግብዓት በ COVID-19 ወቅት በተጽዕኖው ለተጠቁ የማህበረሰብ አባላት እና በአቅራቢያ ካሉ የምግብ ባንኮች አገልግሎቱን ማግኘት ላልቻሉ ነው። የሚችሉ ከሆነ በአቅራቢያዎ ካለ የምግብ ባንክ ይውሰዱ-- ቦታዎችን እና ሰአቶችን ለማወቅ እና ለተጨማሪ መረጃ ሁለት-አንድ-አንድ ወይም https://foodlifeline.org/need-food/. ይጎብኙ።

ስለዚህ ፕሮግራም ጥያቅ ወይም አስተያየት ካልዎት በሶስት ቀን ውስጥ ስለምትመልስ እባክዎን Claire Brownን በኢሜይል clairebrown@uwkc.org ወይም በስልክ (206) 461-6915 ያግኙ። ምናልባት አጥጋቢ መፍትሄ ካላገኙ Leah Rapalee ን በኢሜይል leahr@foodlifeline.org ወይም በስልክ (206) 432-3606 ያግኙ።